# እነ "ጆን ጂሃዲ"ን የማያሰርግ የፀረሽብር ህግ

ክፍል አንድ

አዲስ ቶልቻ

03-18-15

ሰሞኑን አንድ አዲስ ያልሆነ ወሬ እንደ አዲስ ሲነገር ሰምተናል። ይህም ከሶስት ዓመት በፊት እስላማዊ አክራሪነትን መነሻ ያደረገ የሽብር ተግባር ለመፈፀም ወደኢትዮጵያ ሰርጎ ሲንቀሳቀስ በቁጥጥር ስር ውሎ ክስ ተመስርቶበት ቅጣት የተወሰነበትን አሊ አዶረስ የተሰኘ እንግሊዛዊ ጉዳይ የሚመለከት ነው። እንግሊዛዊው አሊ አዶረስ አሸባሪ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ የአራት አመት ከመንፈቅ ቅጣት ከተወነበት ከራርሟል፤ ወሬው አሮጌ ነው። እንደአዲስ እንዲነሳ ያደረገው አሊ የበርካታ አውሮፓውያን፣ አሜሪካውያን፣ ጃፓኖች እና ሶሪያውያንን አንገት ዘግናኝ በሆነ አኳኋን ሲቀላ የቆየውና ሰሞኑን ማንነቱ የታወቀው እንግሊዛዊ ጆን ጂሃዲ ጓደኛ መሆኑና ወደኢትዮጵያ የመጣው ለተመሳሳይ ዓላማ መሆኑ ይፋ መውጣቱ ነው።

ከዚያ በፊትማ "ኢትዮጵያ ምንም ያላጠፋውን እንግሊዛዊ አሰረች" እየተባለ ስትወቀስ ነበር። ያም ሆነ ይህ ሌላኛው አንገት ቆራጭ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰዎችን አንገት እየቆረጠ በሽብር ተግባር እስላማዊ መንግስት የመመስረት ህልሙ በህልምነት አክትሟል። አሁን አሊ አዶረሰ ማረሚያ ቤት ነው። ጓደኛው ጆን ጂሃዲ በእውነተኛ ስሙ መሃመድ ኢሙአዚ ግን ኢራቅ ውስጥ የንፁሃንን ሰዎች አንገት እየቀላ ነው።

በሰሞኑ ጉዳይ ዙሪያ ይህን ያህል ብዬ ለመሆኑ የአሊ አዶረስ ባልደረባ ጆን ጂሃዲ በአስፈሪ የሽብር ተግባር ላይ የተሰማራበት እስላማዊ መንግስት ወይም አይ ኤስ ማንነው? ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ አሸባሪ ቡድን ሰረጎ የገባውን አሊ አዶረስና ሌሎች አሸባሪዎችንም መቆጣጠር ያስቻላት ምስጢር ምንድነው? ኢትዮጵያ ያለባት እስላማዊ አክራሪነትን መነሻ ያደረገ ተጨባጭ የሽብር ስጋት ምን ይመስላል? የሚሉትንና ተያያዥ ጉዳዮችን እንመልከት።

በኢራንና በሶሪያ ሰፊ መሬት ተቆጣጥሮ የካሊፌት ግዛት ያወጀው ራሱን እስላማዊ መንግስት ወይም አይ ኤስ ብሎ የሚጠራ ቡድን መራር ፈተና መፍጠር ከጀመረ እነሆ አንድ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ወራት ቀርተውታል። አስላማዊ መንግስት የተሰኘው ይህ ቡድን ከኢራቅና ሶሪያ በተጨማሪ፣ በሊቢያ ምስራቃዊ አካባቢ፣ በግብፅ የሲናይ ሰርጥ፣ እንዲሁም በሌሎች የመካከለኛው ምስራቅ ሃገራት፣ በሰሜን አፍሪካ፣ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ ኢሲያ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ራሱን እስላማዊ መንግስት ብሎ የሰየመው ቡድን ከድል በኋላ ይኖረኛል በሎ ያመነው ግዛቱ ኢትዮጵያንም ያካትታል።

ይህ እስላማዊ መንግስት የተሰኘ የአክራሪዎች ስብስብ በአውሮፓውያን አቆጣጠር ሰኔ 2014 ዓ/ም ላይ ራሱን ካሊፌት ብሎ መሰየሙን ተከትሎ *አቡ በከር አል ባግዳዲ* የተሰኘን ግለሰብ በከሊፋነት ቀብቷል። እስላማዊ መንግስት መሰረትኩ ያለው በአቡ በከር አልባግዳዲ ከሊፋነት የሚመራው ግዛት በተባበሩት መንግስታትና በዓለም መንግስታት በተናጥል ተቃውሞ ቀርቦበታል፤ እስካሁን ለዚህ ከሊፌት እውቅና የሰጠ አንድም መንግስት የለም። ቡደኑ እውቅና የተነፈገው ከዚህ ቀደም በተለያየ ስያሜ

ሲንቀሳቀሱ በቆዩ አክራሪ እስላማዊ ቡድኖችም ጭምር ነው። ቡድኑ እንደ ካሊፌት “በሙስሊሙ ዓለም የሃይማኖት፣ የፖለቲካና ወታደራዊ የበላይነት ሊኖረኝ ይገባል” ባይ ነው። ከዚህ በመነሳት በሙስሊሙ ዓለም አሁን ለሚገኙት መንግስታት፣ ኤሚሬቶችና ሌሎች ቡድኖች እውቅና አይሰጥም። በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች እነዚህ ተቋማትና ቡድኖች ተቀባይነት እንደማይኖራቸው አውጇል።

በርካታ እስላማዊ የሆኑና ያልሆኑ የዓለም ማህበረሰቦች ቡድኑ እስላምን እንደማይወክል በይፋ አሳውቀዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ እስላማዊ መንግስት ብሎ ራሱን የሚጠራውን ቡድን በጦር ወንጀለኝነትና በሰብአዊ መብት ጥሰት ወንጀሎች ተጠያቂ አድርጎታል።

አሁን ዓለምን እየተፈታተነ የሚገኘው ይህ ራሱን እስላማዊ መንግስት ብሎ የሚጠራ ቡድን የተፀነሰው እ ኤ አ በ1999 ዓ/ም መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህ ወቅት ቡድኑ *አቡ ሙሳብ አልዛርቃዊ* በተባለ ግለሰብ *ጀመአተል ዋ አል ጂሃድ* በሚል ስያሜ ነበር የተመሰረተው። በ2004 ዓ/ም ቡድኑ መጠሪያውን ወደ *ታንዚም ቃኢዳት ፊ ቢላድ አልራፍዳይን* ለወጠ። ይህ መሰረቱን ሞሶፖታሚያ አካባቢ ያደረገ ቡድን “የኢራቅ አል ቃይዳ” በመባል ይታወቅ ነበር። ይሁን እንጂ ቡድኑ አንዴም ራሱን በዚህ ስያሜ ጠርቶ አያውቅም።

በ2006 ዓ/ም ቡድኑ ከሌሎች የኢራቅ አማፂ ቡድኖች ጋር ተቀላቅሎ የሙጃሃዲን ሹራ ካውንስል መመስረቱን አወጀ። ቀደምት የቡድኑ መስራች አልዛርቃዊ በዚሁ ዓመት ተገደለ። በዚሁ 2006 ዓ/ም ማገባደጃ ላይ የሙጃሃዲን ካውንስሉ ከሌሎች ተጨማሪ አማፂ ቡድኖች ጋር በመዋሃድ “የኢራቅ እስላማዊ መንግስት (አይ ኤስ)” በሚል ስያሜ ተደራጀ። ሚያዚያ 2013 ዓ/ም ላይ ወደሶሪያም ተስፋፍቶ ራሱን “የኢራቅና የሶርይ እስላማዊ መንግስት (አይ አስ አይ ኤስ)” ብሎ ሰየመ። በመጨረሻም ከስምንት ወራት በፊት ሰኔ 2014 ዓ/ም ላይ ራሱን እስላማዊ መንግስት (አይ ኤስ) ብሎ ሰይሞ ዓለም አቀፍ ካሊፌት መሆኑን አወጀ።

እንግዲህ ይህ ቡድን ነው አሁን ኢራቅና ሶርያ ውስጥ ሰፊ መሬት ተቆጣጥሮ የሽብር እጁንም ወደአውሮፓ እያዘለቀ፣ በአጋጣሚ በእጁ የገቡትን ምዕራባውያን አንገት እየቀላ የዓመቱ የዓለማችን የትኩረት ማረፊያ የሆነው። በእስላማዊ መንግስት (አይ ኤስ) መሬታቸውና የተፈጥሮ ሃብታቸው ከተያዘባቸው ኢራቅና ሶርያ በተጨማሪ ቡድኑ የዓለም አቀፍ አሸባሪነት ባህሪ ስላለው አሜሪካ መራሽ የመንግስታት ጥምር ሃይል ጥቃት እየሰነዘረበት ይገኛል። ይህ ጥቃት ለወራት የዘለቀ ቢሆንም የተገኘ ለውጥ ግን የለም።

ራሱን እስላማዊ መንግስት ብሎ የሰየመውና ኢራቅና ሶሪያ ላይ መሰረቱን የጣለው ቡድን ከ80 ያህል ሃገራት የተወጣጡ ብቻ 20 ሺህ ገደማ ሰራዊት እንዳለው ይገመታል። አጠቃላይ ሰራዊቱ በመቶ ሺህ የሚቆጠር እንደሆነ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት። ከእነዚህ ከየሃገሩ ከተወጣጡ ተዋጊዎች መሃከል ከ3400 በላይ የሚሆኑት ከምዕራብ አውሮፓ ሃገራት የሄዱ ናቸው። አሁን ቡድኑ ለአውሮፓ ሃገራትና ለአሜሪካ ትልቅ የሽብር ስጋት ሆኗል።

ከሁለት ወራት በፊት በፈረንሳይ የተፈፀመውና ለአስራ ሰባት ንፁሃን ዜጎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የሽብር ጥቃት በአይ ኤስ አባላት የተፈፀመ ነበር። አይ ኤስ ለሽብር ጥቃቱ ሃላፊነት መውሰዱም ይታወቃል። ከአራቱ የፈረንሳይ የሽብር ጥቃቱ ፈፃሚዎች መሃከል፣ ሃያት ቦሜዴን የተባለችው ሴት አሸባሪ ሶርያ ገብታ ቡድኑን መቀላቀሏም ይታወቃል። በርካታ የምእራብ አውሮፓ ሃገራት ዜግነት ያላቸው ሰዎች በእስላማዊ ፅንፈኝነት አመለካከት ተጠምቀው ቡድኑን ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ የሽብር ጥቃት ስጋቱን ሃያል አድርጎታል።

ጥቁር ጭንብል አጥልቆ ለተለያየ ተግባር ሲንቀሳቀሱ በቁጥጥር ስር የዋሉ አሜሪካውያንን፣ አውሮፓውያንንና ጃፓናውያንን አንገት የቀላው መልአከ ሞት - ጆን ጂሃዲ ዜግነቱ እንግሊዛዊ ነው። ይህ፤ ስቴቨን ስትሎፍ፣ ጀምስ ፎሌይና ፒተር ካሲንግ የተባሉ አሜሪካውያንን፣ ዴቪድ ሃየንስና አለን ሄኒንግ የተሰኙ እንግሊዛውያንን፣ ሃሩን ቶኮዋና ኬነጂ ጎቶ ጆጎ የተሰኙ ጃፓናውያንን እንዲሁም ሃያ አንድ የሶርያ ወታደሮችን አንገት መቅላቱን በሁድኑ ይፋ ባደረገው ቪዲዮ ያረጋገጠለት ጆን ጂሃዲ እንግሊዛዊ ዜግነት ያለው መሆኑ በእንግሊዝና በተቀሩት የአውሮፓ ሃገራት ታላቅ ድንጋጤን ፈጥሯል።

እንግሊዛዊው መልአከ ሞት ጆን ጂሃዲ እውነተኛ ስሙ መሃመድ ኢሙአዚ ነው። ትውልዱ ከኢራቃዊያን ቤተሰቦች ሲሆን የተወለደው እ ኤ አ ነሃሴ 17፣ 1988 ዓ/ም ኩዌት ውስጥ ነው። ኢሙአዚ የስድስት ዓመት ልጅ ሳለ ቤተሰቦቹ ይዘውት ወደእንግሊዝ ይገባሉ። ህፃኑ ሙአዚን የእንግሊዛዊ ዜግነትንን ያገኘው በዚህ አጋጣን ነበር፤ የዛሬ 21 ዓመት። ከቤተሰቦቹ ጋር በእንግሊዝ ሰሜን ኪንግስተን መኖር የጀመረው ኢሙኣዚ፣ በሰሜን ኪንግስተን የቅድስት መቅደላዊት አንድኛ የመጀመሪያ ደረጋ ትምህርት ቤት ገብቶ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተከታትሏል። በመቀጠልም ኬይንሰቶን ኮሚኒቲ አካዳሚ ገብቶ ትምህርቱን ተከታትሏል። በመጨረሻም በዌስት ሚኒስቴር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽን ሲስተምና ቢዝነስ አስተዳደር ተምሯል። ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ በኩዌት የአይ ቲ ኩባንያ ውስጥ በሽያጭ ሰራተኝነት ስርቷል።

የመልዓከ ሞቱ ጆን ጂሃዲ ወይም እንግሊዛዊው መሃመድ ኢሙአዚ የአሸባሪነት እንቅስቃሴ ታሪክ የሚጀምረው ከ2009 ዓ/ም መሆኑን መረጃዎች ያመለከታሉ። ከሌሎች ሁለት ጓደኞቹ ጋር - አሊ አዶረስ የተባለ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እንግሊዛዊና ማርሴል ሽሩደል የተባለ ሃይማኖቱን ወደእስልምና የለወጠ ጀርመናዊ ጋር በመሆን ታንዜኒያ የሚገኘውን የዱር አራዊት መኖሪያ ፓርክ ለመጎብኘት ብለው ወደታንዚኒያ ተጉዘው ከነበረበት ወቅት የሞሃመድ ሙአዚና የጓደኞቹ የሽብር ታሪክ የሚነሳው። የዚህ ጉዞ ዓላማ በምስራቅ አፍሪካዊቷ ሃገር ሶማሊያ የሚንቀሳቀሰውንና ኢትዮጵያን ዒላማው ያደረገውን የአፍሪካ የአልቃይዳ ክንፍ የሆነውን አልሸባብ መቀላቀል ነበር። ይህን እንጂ በወቅቱ ይህን አላማቸውን ማሳካት አልቻሉም። የታንዛኒያ መንግስት ኢሙአዚንና ጓደኞቹን የሃገሪቱን መሬት እንደረገጡ አንጠልጥሎ በመጡበት አውሮፕላን መልሷቸዋል። ወደመጡበት እንዲመለሱ የተደረገበት ምክንያት በበረራ ላይ ሰክረው መንገደኞችን ሲረብሹ የነበረ መሆኑ መሬት ከወረዱ በኋላም ከሰጥታ አስከባሪዎች ጋር በመጋጨታቸው መሆኑ ቢነገርም “አይነውሃቸው ስላላማረው ነው” የሚሉም አሉ።

በዚህ አኳኋን የተጀመረው የሶስቱ ሰዎች እስላማዊ አክራሪነት ላይ የተመሰረተ አሸባሪነት ኢሙአዚንን ከአይ ኤስ ጋር ሲቀላቅለው ትውልደ ኢትዮጵያዊው አሊ አዶረስ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀስቅሶ የነበረውን የአክራሪነት እንቅስቃሴ መድረሻው አደረገ። ጀርመናዊው ጓደኛቸው የት እንደሚገኝ እስካሁን የተነገረ ነገር የለም።

ቢቢሲ በቅርቡ ባሰራጨው ዘገባ እንግሊዛዊው ኢሙአዚ በ2006 ዓ/ም ወደሶማሊያ ተጉዞ አልሸባብን ተቀላቅሎ ከነበረና በእንግሊዝ መንግስት ክትትል ስር ከነበረ ግለሰብ ጋር ግንኙነት እንደነበረው አስታውቋል። በሶማሊያ ውስጥ ለሚንቀሳቀሰው አልሸባብ "የቅስቀሳና ገንዘብ የማሰባሰብ ተግባር ላይ ተሰማርቶ ነበር" የሚል ጥርጣሬ መኖሩንም ነው ቢቢሲ በዘገባው ያስታወቀው። ይሁን እንጂ የእንግሊዝ መንግስት ዜግነቱ እንግሊዛዊ መሆኑንና እውነተኛ ስሙም መሃመድ ኢሙአዚ መሆኑን ያረጋገጠው ጆን ጂሃዲን አስቀድሞ አሁን እየፈፀመ ካለው አሰቃቂ የሽብር ጥቃት ማስቆም አልቻለም። እንግሊዛዊ ዜግነት ያለው፣ እንግሊዝ ውስጥ ያደገውና የተማረው ኢሙአዚ ይኸው እንግሊዛውያንን ጨምሮ የሰዎችን አንገት እየቀላ ነው።

ከአንገት ቀይው ጆን ጂሃዲ - እንግሊዛዊው ኢሙአዚ ጋር በአክራሪነትና በሽብርተኝነት የተጠመቀውና ሙአዚ ወደኢራቅ ሲሄድ ተመሳሳይ እስላማዊ መንግስት የመመስረትና ለዚህ ዓላማ ስኬት አንገት መቅላትን ጨምሮ የሽብር ጥቃት ለመፈፀም ወደኢትዮጵያ የተጓዘው አሊ አዶረስ የአንድ ሰው ህይወት እንኳን ሳያጠፋ በቁጥጥር ስር ውሎ ፍርድ ቤት ተገትሯል፤ እ ኤ አ በ2013 ዓ/ም። እንግሊዛዊው አሊ አዶረስ በፍርድ ቤት ቅጣትም ተወስኖበታል።

ኢትዮጵያ ከሰባት ዓመት በፊት ላፀደቀችው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ መነሻ የሆነ ጠንካራ የፀረሽብር ህግ ያላትና የተራቀቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም የደህንነት ሃይል ያላት እንግሊዝ አሸባሪ መሆኑን የሚጠቁም ግልፅና ተጨባጭ ማስረጃ የነበረውን ኢሙአዚ መቆጣጠር አልቻለችም። የኢትዮጵያ የፌደራል ፖሊስና የፀረሽብር የጋራ ግብረ ሃይል ግን በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ዓላማ አንገት መቅያ ካራ ይዞ  የመጣውን የጆን ጂሃዲ ጓደኛ አሊ በቁጥጥር ስር አውሏል። ኢሙአዚ ከእንግሊዝ የደህንነት ሃይል እይታ እንዳመለጠው አሊ ከኢትዮጵያ የደህንነት ሃይል እይታ መሰወር አልቻለም።

የአነገት ቀዪው አሸባሪ ጆን ጂሃዲ ወይም የእንግሊዛዊው ኢሙአዚ ጓደኛና የዓላማ አባሪ የነበረው አሊ አዶረስ በ2013 ዓ/ም በቁጥጥር ስር ውሎ በፌደራል አቃቢ ህግ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ መስርቶበታል። ጥፋተኝነቱ በመረጋገጡ የአራት ዓመት ከስድስት ወር የእስር ቅጣት ተወቀስኖበት የእስር ግዜውን ብመፈፀም ላይ ይገኛል። ብዙዎች በአሊ አዶረስ ላይ ፍርድ ቤት በወሰነው ቅጣት ላይ ቅሬታ አላቸው፤ እጅግ አንሷል የሚል። የቀረበበትን የጥፋተኝነት ማስረጃና ተከሳሹ አሊ ያቀረበውን የመከላከያ ማስረጃ ሳልመለከት በዚህ ጉዳይ ላይ ብዘአስተያየት መስጠት ይከብደኛል። አጠቃላይ ሁኔታው ግን "የተወሰነበት ቅጣት አንሷል" የሚለውን የሚያመለክት ሆኖ ይሰማኛል። ይህን ለሌላ ግዜ እንተወው።

እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው አውሮፓዊ ዜግነት ያላቸው አክራሪ አሸባሪዎች አውሮፓ ውስጥ ከደህንነት ሃይሎች እይታ ውጭ መንቀሳቀስ ከመቻል ባሻገር፣ አውሮፓን የአክራሪነት መጠመቂያና መሰማሪያ መሰረት እያደረጉ መሆኑን ነው። ኢትዮጵያም የእነዚህ በአውሮፓ በአክራሪነት ተጠምቀው የተሰማሩ አሸባሪዎች መድረሻ ለመሆን መብቃቷን እንግሊዛዊው አሸባሪ አሊ አዶረስ አስረጂ ነው።

እርግጥ ኢትዮጵያ እስልምናን ሽፋን ባደረጉና በሌላ ፅንፈኛ አመለካከት ላይ ተመስርተው በሚንቀሳቀሱ ቡድኖች የሽብር ጥቃት ዒላማ ከሆነች ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል። ከሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ ባለው ግዜ ውስጥ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት መጥፋት፣ በመቶዎች ለሚቆጠሩ አካል መጉደል ምክንያት የሆኑ በርካታ የሽብር ጥቃቶች ተፈፅመዋል። ባለፉ አምስት ስድስት ዓመታት ውስጥ ግን የአሸባሪዎች ዒላማ መሆኗ ባይቀየርም ጉዳት ያደረሱ ጥቃቶች ግን አልተፈፀሙም።

ይህ የሆነው ኢትዮጵያ ላይ የሽብር ጥቃት የመፈፀመ ዓላማ ያላቸው ቡደኖች ሰለሌሉ ወይም በፊት የሽብር ጥቃት ሲፈፅሙ የነበሩት እጃቸውን ስለሰበሰቡ አይደለም። አሜሪካና አወሮፓ ውስጥ አሸምቀው ወደኢትዮጵያ የሚዘምቱ ግንቦት 7፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) የመሳሰሉ አሸባሪዎች፣ እነዲሁም ከእነዚህ ጋር ቀጥተኛና የእጅ አዙር ግንኙነት ያላቸው ጥቃቅን የሽብር ቡድኖች ኢትዮጵያ ላይ ግልፅ የሽብር ጥቃት አወጀው እየተነቀሳቀሱ የገኛሉ። አመቺ ሁኔታ ካገኙ በማንኛውም ሰአትና ስፈራ የሽብር ጥቃት ከመፈፀም ወደኋላ አይሉም።

እንግዲህ ኢትዮጵያ የበርካታ አሸባሪዎች ዒላማ ብትሆንም በተለየ ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ጥቃት ተፈፅሞባት አያውቅም። ይህ የሆነው ቀደም ሲል እነደገለፅኩት እጃቸውን ሰብስበው ወይም እነደቢጋ ጉም ድንገት በነው ስለጠፉም አይደለም። ከዚህ ይልቅ አሸባሪዎችን ለመከታተልና የሽብር ጥቃቶችን ከመፈፀማቸው በፊት ማምከን የሚያስችል የፀረሽብርተኝነት ህግ አፅድቃ ተግባራዊ ማድረጓ ቀዳሚው ምክንያት ነው። አሸባሪዎችን ውስጡ የማይሸሽገው ህዝብና ትጉህ የደህንንት ሰራተኞች ድርሻም ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው።

አዚህ ላይ፣ በጣም የሚያስገርምና የሚያሳዝነው ኢትዮጵያ ከምእራባውያኑም ቀድሞ በርካታ የሽብር ጥቃት የተፈፀመባት ሃገር ሆና ሳለ፣ አሁንም በርካታ አሸባሪዎች የሽብር ጥቃት ለመፈፀም የሚያስችላቸውን ቀዳዳ ፈሊጋ በሚቅበዘበዙበት ሁኔታ፣ አሸባሪዎቹን መከላከል ያስቻላትን የፀረሽብርተኝነት ህግ እንድትሰርዝ ወይም ያንዣበበባትን የሽብር ድርጊት ባህሪ ባላገናዘበ ሁኔታ እንድታለዝብ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነን በሚሉ የምእራባውያን መንግስታትና የባለፀጎቻቸው ተላላኪዎች የማያቋርጥ ንዝነዛ የሚሰነዘርባት መሆኗ ነው።

ይህ ብቻ አየደለም፤ በተጨባጭ ማስረጃ የሽብር ድርጊት ለመፈፀም ሲንቀሳቀሱ እንዲሁም የሽብር ድርጊት ፈፅመው የተያዙና የተከሰሱ፣ ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦ ቅጣት የተወሰነባቸው ግለሰቦችን ጭምር እንድትፈታ የሚጠይቁ፣ እስሩ የሰበአዊ መብት ጥሰት እነደሆነ አስመስለው የሚያቀርቡ መግለጫዎችና ዘገባዎች ሲንጋጉባት ቆይታል። የእንግሊዛዊው አንገተ ቀጭ ጆን ጂሃዲ ጓደኛ የሆነውንና ለተመሳሳይ ዓላማ ወደኢትዮጵያ የገባውን እንግሊዛዊ አሊ አዶረስ በቁጥጥር ስር ወሎ በፍርድ ቤት ቅጣት ተወሰኖበት ማረሚያ ቤት መወረዱን የእንግሊዘ የመገናኛ ብዙሃን፣ አንድ እንግሊዛዊ ዜጋ ላይ እንደተፈፀመ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲያቀረቡት እንደነበረ ይታወሳል። የእንግሊዝ መንግስት በገነዘብ የሚደግፋት ኢትዮጵያ አሸባሪውን አሊ አዶረስን ማሰርዋን እንደድፍረት በመቁጠረ የእንግሊዝ መንግስት ዜጋውን ለማስፈታት ኢትዮጰያ ላይ ጫና እንዲያሳድር የወተወቱም

ነበሩ። እርግጥ ዘግይተውም ቢሆን እንግሊዞቹ ኢትዮጵያ በቁጥጥር ስር አውላ ቅጣት የወሰነችበት የጀን ጂሃዲ አጋርና ለተመሳሳይ ዓላማ ሰርጎ የገባው ግለሰብ መሆኑን ተገንዝባለች።

ያም ሆነ ይህ፣ ኢትዮጵያ በተጨባጭ ያሉትን የአሸባሪዎችን ጥቃት ተከላክላ የህዘቧን ሰበአዊ መብት መከበርና ብልፅግና ለመረጋገጥ የፀረሽብርተኝነተ ህጓ ያስፈልጋታል። ኢትዮጵያ የምእራባውያኑ የሽብር ጥቃት ስጋት የሆነው ኢስላማዊ አክራሪነት ላይ የተመሰረተ የሽብረ ጥቃት ኢላማ ነች። ምእራባውያኑና ተላላኪዎቻቸው ይህን ተገንዝበው የፀረሽብርተኝነት ህጉ ላይ የሚያንፀባረቁትን የተቃውሞ አቋምና አዝማሚያ መተው ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያ ያለባትን ከምእራባውያኑ ጋር ተመሳሳይ የሆነ እስላማዊ አክራሪነት ላይ የተመሰረተ የሽብር ጥቃት ለመረዳት ባለፉት አመታት የነበሩ እንቅስቃሴዎችን እናስታውስ።

እንግዲህ፤ እስልምናን ሽፋን ያደረጉ አክራሪ አሸባሪዎች እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለማችን የተለመደ ሁነት መሆን ከጀመረ አመታት ተቆጥረዋል። በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ዓለም አቀፍ ትስስር የመሰረቱ ባልተማከለ ሁኔታ በየአገሩ የሚንቀሳቀሱ በርካታ አሸባሪ ቡድኖች ተፈጥረዋል። ዓለማችን በእነዚህ አክራሪ አሸባሪዎች ሰላም ከራቃት ከራርሟል። በየእለቱ በእነዚህ አሸባሪዎች ጥቃት ህይወት ይጠፋል። ሌሎች የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ይፈጸማሉ። አሸባሪዎቹ በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ሰዎች ሁሌም በስጋት ውስጥ ነው የሚኖሩት። ጠዋት ወጥተው ማታ መግባታቸው ምንም ዋስትና የለውም፤ ለዕድል የሚተው ነው።

አሁን በዓለማችን ላይ ያለው ቀንደኛ አሸባሪ ራሱን እስላማዊ መንግስት ብሎ የሚጠራው ቡድን እና አልቃይዳ ናቸው። ወደ አፍሪከና በተለይ ኢትዮጵያ ወደምትገኝበት የምስራቅ አፈሪካ ቀጠና ስንመለስ ደግሞ አልቃይዳ የፈጠራቸውን አልሸባብንና የአልሸባብ ውላጆች የሆኑ ቡድኖችን እናገኛለን።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ የአልቃይዳ የአፍሪካ ክንፍ ተጠሪ የነበረው ሳሊህ ናባሂል የተባለ ግለሰብ “በምስራቅ አፍሪካ የጂሃድ ጦርነትን ለማስፋፋት በአንድ ግንባር ከመዋጋት ይልቅ በርካታ ያልተማከሉ የሽብር ግንባሮች በቀጠናው ሃገራት መፈጠር አለባቸው” የሚል አቋም ይዞ ነበር። ሳሊህ ናባሂል በ2001 ዓ/ም በአሜሪካ የአውሮፕላን ድብደባ ከመገደሉ በፊት። ይህን ተከትሎ በ2002 ዓ/ም አልቃይዳ ይሸነፋል። ከዚህ በኋላ በሦማሊያ ሲንቀሳቀስ የነበረው የአልቃይዳ የአፍሪካ ክንፍ የሆነው አልሸባብ ሳሊህ ናባሂል ይዞት የነበረውን ያልተማከለ የሽብር እንቅስቃሴ የማደራጀት አካሄድ አስፈላጊነት አመኖበት ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል።

በዚህ መሰረት መካከለኛ ምስራቅን ማዕከሉ ያደረገ የሽብር እንቅስቃሴ ከምስራቅ አፍሪካም ተሻግሮ የምእራብ አፍሪካና ሳህል በረሃ አካባቢ አገራት ላይ ስጋት መጣሉ ይታወቃል። በማሊ አልሳርዲን የተባለው አክራሪ አሸባሪ ቡድን ያደረሰውን ውድመት ብዙዎቻችን እናስታውሳለን። ሞጀአና አዝዋድ የተባሉ አሸባሪ ቡድኖችም በመግርብና ሳህል በረሃ አካባቢ የፈጠሩት ስጋትም እንዲሁ አይዘነጋም። በናይጀሪያ ቦኮሃራም የተሰኘው ቡድን በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በሚፈፅማቸው ተደጋጋሚ የሽብር ጥቃቶች ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነው። በናይጀሪያ በበዙ ሺህ የሚቆጠሩ ነፁሃን የቦኮ ሃራም የሽብር ጠቃት ዒላማ ሆነዋል።

ኢትዮጵያም ባለፉ ጥቂት ዓመታት የዚህ ያልተማከለ የአልቃይዳ የሽብር ቡድን መደራጃና መንቀሳቀሻ ዒላማ ከመሆን አላመለጠችም።

ከሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ሦማሊያ ውስጥ በአልሸባብ ሰልጥኖ ኢትዮጵያ ውስጥ የጂሃድ ቡድን ለማደራጀት ሲንቀሳቀስ የነበረውን ሃሰን ጃርሶ በተባለ ኬንያዊ የሚመራ "ቡሳ ሰገል" የተባለ ቡድን እናስታውሳለን። "ቡሳ ሰገል" የተሰኘው የጅሃድ ቡድን መሪ ሃሰን ጃርሶ ኦሮሚያ ውስጥ ባሌ አካባቢ ለጂሃድ እንቅስቃሴ አመቺ ሥፍራ ለመምረጥና መሳርያ ለማሰባሰብ፣ እንዲሁም የጅሃድ ተዋጊዎችን ለመመልመል በዝግጅት ላይ እያለ፣ ብሄራዊ የመረጃ ደህንነት አገልግሎትና የፌደራል ፖሊስ የጋራ የፀረ ሽብር ግብረሃይል ደርሶበት ከነግብረአበሮቹ በቁጥጥር ስር ውሏል። ሃሰን ጃርሶ በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶበት ጥፋተኝነቱን አምኗል። አቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃም ጥፋተኝነቱ በማረጋገጡ ከነግብረአበሮቹ ቅጣት ተወስኖበታል።

የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ በተመሳሳይ አንድ አሸባሪ የጂሃድ ቡድን በእንቅስቀሴ ላይ እያለ የተደረሰበተ መሆኑም የታወሳል። ይህም ደቡብ ወሎን መሰረቱ አድርጎ ሲንሳቀስ የነበረው "ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን" የተባለ የአልቃይዳ አልሸባብ ውላጅ ቡድን ነው። ይህ አሸባሪ ቡድን እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት ተደርሶበት አደራጆቹና መሪዎቹ በቁጥጥር ሥር ውለው አሁን የክስ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

ቡድኑን በማደራጀትና በመምራት የአሸባሪነት ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የዋሉ ግለሰቦች "ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን" የተባለውን ቡድን አመሰራረት ሂደት አስመልክተው ለፖሊስ መረጃ ሰጥተዋል።

በዚህ መሰረት ዓለም አቀፉ የአሸባሪዎች አውራ የሆነው አልቃይዳ በምስራቅ አፍሪካ ያልተማከለ የሽብር ግንባር ለመመሰረት ባቀደው መሰረት፣ ኬንያ ናይሮቢ አንድ የህቡዕ ቡድን ተደራጅቷል፤ "ዳሩ ቢላል" የሚባል ። አልቃይዳ፣ "ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን" የተሰኘውን የሽብር ቡድን ለማደራጀት ዳሩ ቢላልን እንደድልድይ ተጠቅሟል። ዳሩ ቢላል የተባለው ቡድን ናይሮቢ በሚገኙ የአክራሪነት ዝንባሌ ያላቸው ስድተኞች የተመሰረተ ቡድን ነው። ይህ ቡድን በዋናነት በምስራቅ አፍሪካ ሃገራት ያልተማከለ የሽብር ግንባር ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ቡድኖችን ከአልሸባብና አልቃይዳ ጋር የማገናኘት ሥራ የሚሰራ ነው።

አሁን ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለው "ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን" የተባለው ቡድን አደራጅና መሪ አማን አሰፋ ወይም በተጨማሪ ሥሙ እስማኢል አሰፋ የተባለ ኢትዮጵያዊ ተጠርጣሪ፣ ለፖሊስ በሰጠው ቃል መሰረት፣ በመጀመሪያ ናይሮቢ ከሚገኘው ዳሩ ቢላል የተሰኘ ቡድን ጋር ነበር የተገናኘው። ከዚያ በዚህ ቡድን አማካኝነት ወደ ሦማሊያ ተሻግሮ መሰረታዊ የሽብርና የወታደራዊ ሥልጠና እንዲወስድ ተደርጓል። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ራሳቸውን የቻሉ የሽብር ቡድኖችን በማሰልጠንና በማደራጀት በመሳሪያ የተደገፈ "የጅሃድ ጦርነት" የሚል ሥያሜ የተሰጠው የሽብር ጥቃት ለመሰንዘር የሚያስችለውን ሥልጠና እንደጨረሰ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል።

አማን ወይም እስማኤል አሰፋ ከሶማሊያ እንደተመለሰ እንቅስቃሴውን የጀመረው በአዲስ አበባ እንደነበር ገልጿል። በአዲስ አበባ መርካቶ ሃደሬ ሰፈር አካባቢ በስውር ሊያካሂደው ላሰበው እንቅስቃሴ ያመቸው ዘንድ "ሰለፊያ" የተሰኘ ጭማቂ ቤት ይከፍታል። በዚህ ለሽፋን በተቋቋመው ጭማቂ ቤት ወጣቶችን በማሰባሰብ "ጀማአተል ተውሂድ" የተባለ የጂሃድ ዓላማን የሚያስፋፋ ቡድን ያደራጃል።

ከዚህ ቡድን አባላት መሃከል የተወሰኑት ወደ ናይሮቢ ተጉዘው "ዳሩ ቢላል" የተባለውን ቡድን ከተቀላቀሉ በኋላ፣ የአዲስ አበባውን የጂሃድ ቡድን ከአልሸባብ ጋር ማገናኘት ጀመሩ። በስተመጨረሻም ይሄው "ሰለፊያ" ጭማቂ ቤት ውስጥ የተመሰረተው "ጀመአቱል ተውሂድ" የተሰኘ ቡድን በደቡብ ወሎ አካባቢ መቀመጫውን አድርጎ "ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን" የተባለውን የኢትዮጵያ የአልቃይዳ ግንባርን አደራጀ።

ይህ የአልቃይዳ ግንባር ግን በማሊ ከፍተኛ ጉዳት እንዳመሰው አልሳርዲን፣ ናይጄርያን የጭንቅ ምድር እንዳደረገው ቦኮ ሃራም አልቀናውም፡፡ የብሄራዊ የመረጃ ደህንንትና የፌደራል ፖሊስ የጋራ የፀረ ሽብር ግብረሃይል በሽልነቱ ደረሶበታል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የሽብር ጥቃትን መከላከልን ዓላመው አድርጎ የፀደቀው የኢፌዴሪ የፀረሽብርተኝነት ህግ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

"ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን" የተባለው የኢትዮጵያ የአልቃይዳ/አልሸባብ ግንባር በሽልነቱ ከተጨናገፈ ከአንድ ዓመት በኋላ ደገሞ ማለትም ባለፈው ዓመት  በሁለት የተከፈለ የአልቃይዳ የሽብር ግንባር መሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸው ይታወሳል ፤ ካኦርጃ የተባለ የሽብር ግንባር ።

የብሄራዊ የመረጃ ደሕንነትና አገልግሎትና የፌደራል ፓሊስ የጋራ የፀረሽብር ግብረሃይል ባለፈው ዓመት በጉዳዩ ላይ በሰጠው መግለጫ፣ ካኦርጃ የተባለ ፅንፈኛ የእስልምና አክራሪ አመለካከትን በኃይልና በሽብር ለማስፋፋት በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የሁለት የአሸባሪ ቡድኖች ሃያ አምስት አባላትን በቁጥጥር ሥር ማዋሉን ነበር የገለፀው። በሁለት የህቡዕ ቡድኖች የተደራጁት ተጠርጣሪዎች አልሸባብ ከተባለው ዓለም አቀፉ አሸባሪ አልቃይዳ ጋር ቁርኝት ባለው አሸባሪ ቡድን በጎረቤት አገር ሶማሊያ ውስጥ የሽብር ሥልጠና መውሰዳቸውንም አሰታውቆ እነደነበረ እናስታውሳለን።

አንደኛው ቡድን ቀጥተኛ አመራር የሚያገኘው ደቡብ አፍሪካ ከሚገኝ አንድ አክራሪ ቡድን እንደነበረ፣ የሽብር ቡድኑ በሶማሊያ ሥልጠና ካገኘ በኋላ በኬንያ በኩል ወደደቡብ አፍሪካ በመጓዝ አደረጃጀቱን አጠናክሮ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን እንቅስቃሴ ለመጀመር በዝግጅት ላይ እንዳለ በተደረገ ክትትል አባላቱ በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ነበር መግለጫው ያስታወቀው።

ሁለተኛው የሽብር ቡድን ደግሞ በሱዳን፣ በየመንና በእንግሊዝ በሚገኙ ዓለም አቀፍ የካኦርጃ ጂሃዲስቶች እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት በመመስረት ቀጥተኛ አመራርና ልዩ ልዩ ድጋፍ ሲያገኙ ነበር የቆየው። ይህ ቡድን ሰላሳ ያህል አባላቱን ወደሶማሊያ በመላክ በአልሸባብ አማካኝነት ወታደራዊ ሥልጠና እንዲያገኙ መደረጉንም መግለጫው አመልክቶ እንደነበረ አናስታውሳለን።

የካአርጀ እንቅስቃሴ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሃይማኖት ሽፋን የሚፈፀሙ የሽብር ድርጊቶች ውስጥ የተጋ ተሳትፎ ያለው መሆኑን፣ እንቅስቃሴው የሚከተላቸው የዕምነት መርሆዎች ከናይጄሪያው እስላማዊ ቡድን *ቦኮ ሃራም* እምነቶች ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን መግለጫው አስታውቋል።

ካአረጀ፣ አስተምህሮውን የማይጋሩ ሌሎች ሙስሊሞችን በሙሉ በካሃዲነትና በመናፍቅነት ይፈርጃል። በከሃዲነት የፈረጃቸውን ለመግደል በፈጣሪ የተሰጠ መለኮታዊ ፍቃድ አለኝ ብሎም ያምናል። እንዲሁም ለምድራዊ መንግስት ግብር መክፈልን እንደከፍተኛ ሃጢያትና የዕምነት ጥሰት ይመለከታል። የሞባይል ስልክ ካርድ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚቀረጥበት በመሆኑ “በሞባይል ስልክ መገልገል በእስልምና እምነት የተከለከለ ሃጢያት (ሃራም) ነው” የሚል እምነት አለው። ከዚህ በተጨማሪ የትራፊክ ሕግጋትን ማክበርን ጨምሮ ዘመናዊ ትምህርትን መሻት ወይም መከታተል ለዕርግማን የሚዳርግ ከፍተኛ ሃጢያት አድረጎ በማቀረብ ይህን አመላከከቱን በሌሎች ላይ በኃይልና በተፅእኖ የመጫን ዓላማ አለው።

እንግዲህ ይህ አወሮፓውያኑ ጥብቅ የፀረ ሽብር ህግ እነዲያወጡ ካስገደዳቸው የሽብር ስጋት ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያ የፀረሽብርተኝነት ህጓን እንድትሰርዝ ወይም የአሸባሪዎቹን ባህሪ ባላገናዘበ ሁኔታ እንድታለዝብ መጠየቅ በምንም አመክነዮ ተቀባይነት የሌለው ትልቅ ስህተት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ልክ እነደ አወሮፓ ሃገራት ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ በጂሃዲስቶች የሚመራ የሽብር ጥቃት ፈፃሚዎቹ ከውጭ የመጡ ብቻ ሳይሆኑ አብረውን የሚኖሩና የኢትዮጵያዊነት ዜግነት ያላቸው ናቸው። ይህ ኢትዮጵያ ከፈተኛ የሽብር ተጋላጭነት ስጋት ያለባት ሃገር መሆኗን ያመለክታል።

**ይቀጥላል**